# የረጅም ጊዜ የቤት ባለቤት በመሆንዎ፣ የንብረት ታክሶችዎን መቀነስ ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሃብት ይወቁ።

ቢያንስ ለሰባት ተከታታይ አመታት ነዋሪዎች በዲሲ ውስጥ የቤት ባለቤት በመሆናቸው እና በመኖራቸው የታክስ ክሬዲት ሊያገኙ ይችላሉ። የክሬዲቱ መጠን ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ በከፈሉት የንብረት ታክሶች መጠን ላይ ይወሰናል።

ይህ ክሬዲት የዝቅተኛ ገቢ የረጅም ጊዜ የቤት ባለቤት ክሬዲት (ወይም የሰንጠረዥ ኤል ታክስ ክሬዲት) ይባላል እና የቀረበውም የታክስ እና ገቢ ቢሮ ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ **ሁሉ**መግለጫዎች እውነት ከሆኑ፣ ብቁ ነዎት፡

- በዲሲ ውስጥ ወይም በህብረት ስራ መኖሪያ ቤቶች ማህበር ውስጥ ቤት አለዎት።
- ቢያንስ ለሰባት ተከታታይ አመታት በቤትዎ የኖሩ ከሆነ።
- ቤትዎ የሚገኘው ዲሲ ውስጥ ነው።
- ላለፉት ሁለት አመታት የዲሲ የንብረት ታክሶች ለቤትዎ ከከፈሉ።
- ንብረትዎ የ DC Homestead ቅነሳ ከተቀበለ።
- የቤተሰብዎ አመታዊ አጠቃላይ ገቢ—ታክስ ከመክፈልዎት በፊት ያለው ገቢዎ— ለቤተሰብዎ መጠን ከገደቡ እኩል ወይም በታች ነው። ገቢዎን ለማስላት፣ ባለፈው አመት ያቀረቡትን የታክስ ተመላሽ ይመልከቱ፣ እንዲሁም ይህንን ለማረጋገጥ ከስር ያለውን ሰንጠረዥ ይጠቀሙ።

| **የቤተሰብ መጠን** (ከተከራዮች በስተቀር ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰውን ይቁጠሩ) | **ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ** |
|---|---|
| 1 | $44,100 |
| 2 | $50,400 |
| 3 | $56,700 |
| 4 | $63,000 |
| 5 | $69,300 |
| 6 | $75,600 |
| 7 | $81,900 |
| 8 | $88,200 |

## ያመልክቱ።

- የ ሰንጠረዥ ኤል ቅጽ ያጠናቅቁ።
- ለ Office of Tax and Revenue በ 1101 4th Street SW FL4, Washington, DC 20024 ላይ በየአመቱ ዲሴምበር 31 ላይ በፖስታ ይላኩ።

## ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?

1. እኛ—የዲሲ መንግስት— የእርስዎን ብቁነት እናረጋግጣለን።
2. በ ሰንጠረዥ ኤል ቅጽ ላይ ባለው በመረጡት የመላኪያ ዘዴ ተመስርቶ፣ በቀጥታ ተቀማጭ ወይም በቼክ የታክስ ክሬዲቱን ይቀበላሉ።

ለክሬዲቱ ብቁ እንዳልሆኑ ከደረስንበት፣ በተሞላው የ ሰንጠረዥ ኤል ቅጽ ላይ ባስቀመጡት አድራሻ ማሳወቂያ ይደርስዎታል።

## ሁሉም ብቁ አመልካቾች ክሬዲቱን ያገኛሉ?
አዎ፣ ቅጹ በትክክል እና በወቅቱ ከገባ።

## ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?
በታክስ አመቱ የእርስዎ ቤተሰብ አንድ ክሬዲት ብቻ ያገኛል።

## ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?
መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት የታክስና የገቢ ቡድንን በ (202) 727-4829 ላይ ከሰኞ - አርብ ከ 8፡15am እስከ 5:30 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ደውለው ያግኙ። ወይም በ e-services.otr@dc.gov ላይ “Schedule L” በሚለው ርዕሰ መስመር በመጠቀም ለቡድናችን ኢሜይል ያድርጉ።

## የንብረት ታክሶቼን ለመክፈል አሁንም እርዳታ ያስፈልገኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?
በእኛ ሃብቶች ገጽ ላይ ታክሶችን ለመቀነስ እርዳታ ሊሰጡ ስለሚችሉ ሌሎች ሀብቶች መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
## ክሬዲቱ ለወደፊት የታክስ አመታት ወዲያው ይተገበራል?
አይ። ለወደፊት የታክስ ክሬዲት መቀበል ከፈለጉ፣ የሰንጠረዥ ኤል ቅጽን በየዓመቱ ዳግም ማስገባት አለብዎት።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*